# ሕዝቡን ከወደዳችሁ ፈታችሁ ልቀቁት

ከእስክ ነጻነት
eske.netsanet@hotmail.com

ይህ የአክብሮት ጥሪ በሰላም ስም ለምትንቀሳቀሱና የወያኔ ሰላባ ለሆናችሁ የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ ነው: ጥሪዬን በጽሞና አንብባችሁ የጻፍኩትን ሳይሆን በጽሑፉ መስመር መሀል ያለውን መልዕክቴን እንድትረዱልኝና ተግባራዊ እንድታደርጉልኝ በኢትዮጵያ ህዝብ ስም በታላቅ ተህትና እጠይቃለሁ::

"We can't change the past but we can learn from it for a better future" ያለፈን መቀየር አይቻልም: ያለምክንያት በግፈኞች የረገፈ አጥንትን የፈሰሰ ደምን መመለስ አይቻልም: ሌላ ደም ደግሞ እንዳይፈስ፣ ቢፈስም እንኳ ውጤት ለማምጣት እንዲሆን ማድረግ ግን ይቻላል: እናንተ በአሁኑ ጊዜ እየተከተላችሁ ያለው የፖለቲካ ዘዬ ግን ሌላ ተጨማሪ ደም ያለምክንያት እንዲፈስ ማድረግ ካልሆነ በስተቀር እምባ የሚያብስ አይደለም:

ይህንን ስል ሰላማዊ ትግል ውጤት የለውም ማለቴ አይደለም ግን ከማን ጋር ለማለት ነው: ከጅብ ጋር ተስማምቶ አጥንት መጋራት ይቻላል? ወያኔ እንደዚያ ነው: ስለ ወያኔ ብዙ የተባለ ሰለሆነ እኔ መናገርም የለብኝም:

እስኪ ያለፉትን ክንውኖች እንመልከት: ወያኔን አምነው በሰላማዊ ትግል የተካፈሉትንና በህዝቡና በራሳቸው ላይ የደረሰውን ለአብነት እስኪ አንድ ሁለቱን እንመልከት:

ኦነግ

እንደሚታወቀው ወያኔ የሽግግሩን መንግስት ሲያቋቁም ኦነግ ዋነኛ ተቃዋሚና አብላጫ መቀመጫ የነበረው ድርጅት ነበር: ህዝብም ውስጥ ገብቶ ያደራጀና ሰፊ ድጋፍ የተቸረው ድርጅት እንደነበር ሁላችንም እናውቃለን: የኦሮሞ ህዝብ ኦነግን አቅፎ ኦህዴድን ስለተፋው እንዳውም ዋና የኦህዴድ አባላቱ ሳይቀሩ ኮንዶም አሉን እያሉ በየአደባባዩ ያላዝኑ እንደነበር የምናስታውሰው ነው: ይህም የኦነግ መጠናከርና የወያኔ ስሪት የሆነው ኦህዴድ መዳከም ወያኔን እንቅልፍ ስለነሳውና በዚያ ሁኔታ ቢቀጥልና ወደ ምርጫ ቢኬድ ምን ወሆን እንደሚችል ስለገመተ ኦነግን ከሽግግር መንግስት ማስወጣት ግድ ሆነበት እናም አስወጣው: ሌንጮ ለታ የታሰሩትን አነ አስፋው ዘገዬን ማስፈታትና የባልስልጣናቱን ቤተሰቦች ከሐገር እንዲወጡ ያደረጉት ጥረት ቢሳካም ደጋፊዎቻቸውን ግን ለያደኑ አልቻሉም: ወያኔ እንዳለው ወደ 20,000 የሚጠጉ የኦነግ ወታደሮችን ማረክሁ ብሎ አቅራራ እነ ስዬም እንኳን ጦርነት ማሸነፍ ጦርነት መስራት እንችላለን ብለው ተመጻደቁ: ኦነግ ሽግግር መንግስቱ ውስጥ እያለ ወያኔ የኦነግ ደጋፊዎችን አጥንቶ ስለነበረ በተለያዩ ምክንያት አሰራቸው፣ ገደላቸው፣ አሰቃያቸው: አሁንም ይህ ድርጊት አልቆመም: ኦነግ ወያኔን አምኖ ደጋፊዎቹን በይፋ ባያወጣ ኖሮ ወያኔ ማ ማን ነው ብሎ ለመሰለል ብዙ፣ ብዙ በጠየቀው ነበር: የሚኞች፣ የታሳሪዎች፣ የተሰቃዮች ቁጥርም

በቀነሰ ነበር: እዚህ ላይ አነግ ተሳስቷል ለማለት አይደለም: ወያኔን አምኖ ሽግግር መንግስት ውስጥ ገብቶ ግን በወያኔ ከሃዲኒት በህዝባችን ላይ የደረሰውን ሰቆቃ ለማመልከትና ከዚህ ህዝባችን ስቃይና እልቂት ትምህርት እንድንውስድ ነው::

መአህድ

ወያኔ በሰላማዊ መንገድ ከተደራጃችሁ የፖለቲካ ድርጅት ማቋቋም ትችላላችሁ በማለቱና በበደኖ የተደረገው ዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ እንዳይደገም አንደ ፕሮጀክት የተጀመረው የመአህድ ድርጅት በፕሮፌሰር አስራት ወልደየስ ፕሬዘዳንትነት ተመሰረተ: ወያኔ እንደሚፈልገው መአህድ የተልፈሰፈሰ ድርጅት እንዳማይሆን ቀድሞም ያውቀዋል አጋጣሚውን ግን ማን የውያኔ ጠንካራ ተቃዋሚዎች እንደሆኑ ለማውቅ ያደረገው ነበር: እናም የመአህድን ደጋፊዎች በጅምላ አስረ፣ ደበደበ፣ አሰቃዬ፣ የሞቱ ሞቱ የተሰወሩ ተሰወሩ ፕሬዘዳንቱን ፕሮፌሰር አስራትን: በስር ቤት ህይወታቸው እስኪያልፍ አንገላታቸው፣ አሰቃያቸው: መአህድ ደጋፊዎቹን በግልጽ ባያስተዋውቅ ኖሮ ወያኔ ለስለላ ብዙ ዋጋ ባስከፈለው ነበር: የወያኔን ስራ ግን ተቃዋሚ ድርጅቶች እየሰራችሁለት ነው:

ቅንጅት

ወያኔ ስልጣን ኮርቻ ላይ ከተፈናጠጠ ጀምሮ እንደ ቅንጅት አይነት ጠንካራ ተቃዋሚ ገጥሞት እንደማያውቅ፣ የኢትዮጵያ ህዝብም ሙሉ እምነቱን ያሳደረበት ድርጅት ነበር: ነገር ግን የህዝብ ድጋፍ እንጂ የመከላከያ ዝግጅት አልነበረውም፣ ጦር ሰራዊቱም የኢትዮጵያ ሰራዊት ይሁን የወያኔ እርግጠኛ አልነበረም: (Naïve) ነበር: የሆነ ሆኖ ያ ሁሉ ህዝብ አለቀ: የሚታወቀው አዲስ አበባ የተገደሉት 193 ሰዎች ናቸው: ብላቴ፣ ዴዴሳ፣ ጦላይ፣ እና ሌሎችም ቦታዎች ያለቀውን ወጣት ግን ቤቱ ካልሆነ በቀር ማንም አያውቀውም: አስከሬናቸው እንኳ ለክብር እረፍት አልታደለም: በየበረሃው አውሬና አሞራ ተቀራምቶታል:: በእስር የተሰቃየውም በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ነበር: እናንተም ለሁለት ዓመት በእስር ተሰቃችሁ: ምን ተገኘ? ምንም: እናንተ ህዝብን አደራጅታችሁ ደጋፊያችን ይኸው ባትሉት ኖሮ ወያኔ ማ እንደሚወደው ም እንደሚጠላው የሚያውቅበት ቀመር አይኖረውም ነበር: እና ከዚያ በኋላ ወያኔ የብረት ክንዱን አጠንክሮ እያዋከባችሁ ነው: ቅንጅትን የመሰለ ጠንካራ ድርጅት ይዛችሁ ህዝቡንም ራሳችሁንም ለዚያ ሁሉ ሰቆቃ የዳረጋችሁ፣ አሁን በየበኩላችሁ የተዳከመ ድርጅት ይዛችሁ የትም አይደረስ: ወያኔን ከመጥቀምና ህዝቡንና ራሳችሁን ለሌላ ዙር ስቃይ ለመዘጋጀት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ጥቅም አይታየኝም:: ብርቱካን ከሆነች በዚህም ሆነ በዚያ ትፈታለች: ወያኔም ዋጋውን ያገኛል: ግን በደነበረና በቆሰለ ቁጥር እናንተን ንዴት ማብረጃ እንዳያደርጋችሁ አስቡበት::

**ስለዚህ አገርንና ህዝቡን የምትወዱት ከሆነ ድርጅቶቻችሁን አፍርሱና ያሰራችሁትን ህዝብ ፍቱት: ነጻ አውጡት:**

**ይህ ደግሞ ዘርፈ ብዙ ጥቅም አለው:**

1. ህዝቡ ባልተጨበጠ ብቻ ሳይሆን በማይጨበጥ ትስፋ ታስሮ አይኖርም: ለነጻነቱ ያዋጣኛል የሚለውን የራሱን መንገድ ለመምረጥ ነጻነቱን ሰጣችሁት ማለት ነው:
2. ለሰላማዊ ትግል ምንም ክፍተት እንደሌለ ግልጽ ስለሚሆን ወያኔ ዲሞክራት ነኝ ብሎ ለማለት በሩን ይዘጋበታል እና ማንነቱንና ምንነቱን ቁልጭ አድርጎ ለማሳየት ይጠቅማል
3. እናንተም ህዝቡም ነጻ ትወጣላችሁ: የተጎጂ ቁጥርም ይቀንሳል፣ የወያኔ የሰለላ ውጭ ይጨምራል፣ የስለላ ኃይሉ ይሳሳል:

በቂ መስዋዕትነት ተከፍሏል: እናንተንም በተጨማሪ ማጣት አንፈልግም: ጊዜ ኖሯችሁ ራዕያችሁን በጽሁፍ ለመጪ ትውልድ ብታወርሱ ታላቅ ወለታ ነው ብዬ አምናለሁ::

እግዚአብሄር ኢትዮጵያን ይጠብቅ!